HOLY CROSS HEALTH
A Member of Trinity Health

# የግላዊነት አሰራሮች ማሳወቂያ

ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፦ ኤፕሪል 14፣ 2003
የተሻሻለው፦ ጁን 1፣ 2024

ይህ ማሳወቂያ እርስዎን የሚመለከት የሕክምና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እና ይፋ ሊደረግ እንደሚችል እንዲሁም እርስዎ እንዴት ይህን መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ ነው። እባክዎ በጥንቃቄ ይገምግሙት።

በ1996 በወጣው የጤና መድህን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ድንጋጌ (Health Insurance Portability and Accountability Act) እና በኢኮኖምያዊ እና ክሊኒካዊ ጤንነት የጤና መረጃ ቴክኖሎጂ ድንጋጌ (Health Information Technology for Economic and Clinical Health Act) (በ 2009 በወጣው የአሜሪካ ማገገምያ እና ዳግም-ጥረት ድንጋጌ (American Recovery and Reinvestment Act) አንቀጽ XIII ላይ የሚገኝ) (አንድላይ “HIPAA” ተብሎ የሚጠራ) እንዲሁም በየጊዜ በሚደረጉ ማሻሻያዎች መሰረት የታካሚ ማንነት የሚያጋልጥ የግለሰብ መረጃ ሚስጢር (ይህ መረጃ “ጥብቅ የጤና መረጃ” (protected health information) ሲሆን በዚህ ሰነድ “PHI” ተብሎ ይጠራል) በሚያስጠብቅ አኳሃን እንድንይዝ ግዴታ ተጥሎብናል። በተጨማሪ PHIን በተመለከተ የግላዊነት አሰራሮች ማሳወቂያ ለታካሚዎች እንድንሰጥ ግዴታ ተጥሎብናል። የእርስዎን PHI በስቴት እና በፌደራል ሕግ በተፈቀደው ወይም በተጠየቀው መሰረት ብቻ እንጠቀማለን ወይም ይፋ እናደርጋለን። ይህ ማሳወቂያ እኛ የምናመነጫቸውን የሕክምና መዛግብት ጨምሮ በእኛ ቁጥጥር ስር ያለው የእርስዎ PHI ላይ ይተገበራል።

የጤና መረጃዎ በጣም የግል ጉዳይ እንደሆነ ይገባናል፣ ስለሆነም ግላዊነትዎን ለመጠበቅ በቁርጠኝነት እንሰራለን። እባክዎ ይህን የግላዊነት አሰራሮች ማሳወቂያ በጥንቃቄ ያንብቡት። ይህ የእርስዎን PHI እንዴት እንደምንጠቀምበት እና እንዴት ይፋ እንደምናደርግ ይገልጻል።

ይህ ማሳወቂያ ሆስፒታላች እና የሕክምና ሰራተኞቹ በዋናው ሆስፒታል፣ በተመላላሽ ታካሚ ዲፓርትመንቶች እና ክሊኒኮች ውስጥ የሚሰጡት የጤና እንክብካቤ ላይ ይተገበራል። ይህ ማሳወቂያ የ Trinity Health እንቅስቃሴዎች ላይ እና የ Trinity Health አባል በሆነው ሆስፒታላችን ላይ፣ እንዲሁም በመላ አሜሪካ በሚገኙ ብዙ ግዛቶች ውስጥ ተቋማት ባሉት የካቶሊክ ጤና እንክብካቤ ስርአት ላይ ጭምር ተግባራዊ ይሆናል።

## I. የተፈቀደ መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ

A. **<u>እንክብካቤ፦</u>** የእኛ ሚኒስትሪ የጤና እንክብካቤ ተግባራት ማከናወን ይችል ዘንድ የእርስዎን የጤና እንክብካቤ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለማቅረብ፣ ለማስተባበር፣ ወይም ለማስተዳደር የእርስዎን PHI ይጠቀማል ወይም ይፋ ያደርጋል። የሚከተሉት እኛ የእርስዎን PHI እንዴት እንደምንጠቀም እና/ወይም ይፋ እንደምናደርግ ምሳሌዎች ናቸው፦

i. ለሚከታተሉት ሐኪምዎ፣ ለሚያማክሮት ሐኪምዎ(ሞችዎ)፣ እንዲሁም ለሌሎች የእርስዎ ሕክምና እና እንክብካቤ ይህ መረጃ እንደሚያስፈልጋቸው ብቁ ምክንያት ያላቸው የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች።

ii. የሕክምና እንክብካቤዎትን እኛ እና ሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች እንድናስተባብርልዎ (ለምሳሌ፣ ቀጠሮ ለማስያዝ) ስምዎ፣ አድራሻዎ፣ የስራ ቅጥር ሁኔታዎ፣ የመድህን አቅራቢዎ፣ ወዘተ እንፈልጋለን።

iii. በተቋሞቻችን የሕክምና ወይም ሕክምናዊ እንክብካቤ ቀጠሮ እንዳሎት ለማስታወስ እንድናገኝዎ።

iv. የሕክምና አማራጮች ወይም ሌሎች ሕክምና ነክ ጥቅማጥቅሞች ወይም አገልግሎቶችን የተመለከተ መረጃ እንድንሰጥዎት።

v. በሕግ አስከባሪ መኮንን ስር ማረምያ ቤት ውስጥ ታስረው ከሆነ ያሉት፣ የእርስዎን PHI ለማረሚያ ቤቱ ተቋም ወይም ለሕግ አስከባሪው ባለስልጣን እንሰጣለን።

**B. <u>ክፍያ፦</u>** የእኛ ሚኒስትሪ ለክፍያ አላማዎች የእርስዎን PHI ይጠቀማል እና ይፋ ያደርጋል። የሚከተሉት እኛ የእርስዎን PHI እንዴት እንደምንጠቀም እና/ወይም ይፋ እንደምናደርግ ምሳሌዎች ናቸው፦

i. ለክፍያ አላማዎች ማለትም ሽፋን ለመለየት፣ ለብቁነት፣ ቅድመ-ማስጸደቅ/ ሕክምና ለማስጸደቅ፣ ክፍያ ለመጠየቅ፣ የካሳ ጥያቄ ለማስተዳደር፣ ለገንዘብ ተመላሽ ኦዲቶች፣ ወዘተ ሲባል ለመድህን ኩባንያ፣ ሶስተኛ ወገን ከፋይ፣ ሶስተኛ ወገን አስተዳዳሪ፣ የጤና እቅድ ወይም ለሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ (ወይም ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ተወካዮቻቸው)።

ii. ለሰብሳቢ ኤጀንሲዎች እና ሌሎች የሕክምና ክፍያ በመቀበል ላይ የተሰማሩ ሶስተኛ ወገኖች።

**C. <u>የጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች፦</u>** የእኛ ሚኒስትሪ ለጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች አላማዎች የእርስዎን PHI ይጠቀማል እንዲሁም ይፋ ያደርጋል የሚከተሉት እኛ የእርስዎን PHI እንዴት እንደምንጠቀም እና/ወይም ይፋ እንደምናደርግ ምሳሌዎች ናቸው፦

i. ጤና ከማሻሻል ወይም የጤና እንክብካቤ ወጪዎች ከመቀነስ፣ ከትምህርት፣ የብቃት ማረጋገጫ፣ የስራ ፈቃድ፣ እና ከብቃት ማረጋገጫ እንቅስቃሴዎች ጋር ለሚተሳሰሩ የኬዝ አስተዳደር፣ የጥራት ማረጋገጫ፣ ለፍጆታ፣ አካውንቲንግ፣ ኦዲት፣ የመልቀቂያ እቅድ፣ የህዝብ ጤና እንቅስቃሴዎች።

ii. ለአማካሪዎች፣ የሒሳብ ሰራተኞች፣ ኦዲተሮች፣ ጠበቃዎች፣ የትራንስክሪፕሽን ኩባንያዎች፣ የመረጃ ቴክኖሊጂ እና ክላውድ ማከማቻ አቅራቢዎች፣ ወዘተ።

**D. <u>ለሌሎች ጉዳዮች መጠቀም እና ይፋ ማድረጎች</u>:** ከሕክምና እንክብካቤ፣ ክፍያ፣ እና የጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች ጋር ተያይዞ የእኛ ሚኒስትሪ ለሚከተሉት አላማዎች ጭምር የእርስዎን PHI ሊጠቀም ይችላል፦

i. ለገቢ ማሰባሰብ እና ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች፦ የተወሰነውን የእርስዎ PHI ተዛማጅ ፋውንዴሽኖችን ጨምሮ፣ ለአንዳንድ የገቢ ማሰባሰብያ እና ማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች ልንጠቀምበት እንዲሁም ይፋ ልናደርገው እንችላለን። ለምሳሌ፣ ዲሞግራፍያዊ መረጃዎትን፣ የሕክምና እንክብካቤ ያገኙባቸው ቀናትን፣ ያከሞት ሐኪም መረጃን፣ የአገልግሎት መምሪያ እና የውጤት መረጃ ልንጠቀም ወይም ይፋ ልናደርግ እንችላለን እንዲሁም የገንዘብ ልገሳን ልንጠይቅ እንችላለን። ወደ እርስዎ የተላከ የትኛውም የገቢ ማሰባሰብ እና ማርኬቲንግ ተግባቦት በቀጣይ ጊዜ ተመሳሳይ ተግባቦቶችን <u>ያለመቀበል</u> መብቶችዎን እንዴት እንደሚጠቀሙ ያሳውቅዎታል።

ii. ሜዲካል ምርምር፦ የእርስዎን PHI በተፈቀደ አኳሃን እንጠቀምበታለን እንዲሁም ለጸደቁ የሜዲካል ምርምር ፕሮጀክቶች ይጠቀሙበት ዘንድ ለሚጠይቁ ሜዲካል ተመራማሪዎች አሳልፈን እንሰጣቸዋለን። ተመራማሪዎች የተቀበሉትን PHI በሙሉ ጠብቀው እንዲይዙ ይገደዳሉ።

iii. መረጃ እና የጤና ማስታወቂያ እንቅስቃሴዎች፦ የተወሰነውን የእርስዎ PHI ለአንዳንድ የጤና ማስታወቂያ እንቅስቃሴዎች እንጠቀምበታለን እንዲሁም ይፋ እናደርጋለን። ለምሳሌ፣ ስምዎ እና አድራሻዎ የራስዎ የጤና ችግሮች ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ የዜና መጽሔት ወይም የተወሰነ መረጃ ለእርስዎ ለመላክ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

E. **<u>የበለጠ ጠንካራ የግዛት እና የፌደራል ሕጎች፦</u>** የ [Insert your State] የግዛት ሕግ በብዙ ቦታዎች ካለው HIPAA የበለጠ ጠንካራ ነው። አንዳንድ የፌደራል ሕጎችም ከ HIPAA የበለጠ ጠንካራ ናቸው። የእኛ ሚኒስትሪ ለእነዚህ የበለጠ ጠንካራ የሆኑ የግዛት እና የፌደራል ሕጎች ተገዢ መሆኑን ይቀጥላል።

i. **<u>የበለጠ ጠንካራ የፌደራል ሕጎች፦</u>** የፌደራል ሕጎች እንደ የህጻናት የኦንላይን ግላዊነት ጥበቃ ድንጋጌ (Children's Online Privacy Protection Act) እና የፌደራል ሕጎች እና አልኮል እና የአደንዛዥ ዕጽ ሕክምና የሚመለከት የጤና መረጃ ሚስጢራዊነት የሚያስተዳድሩ ደንቦችን የመሳሰሉ የመረጃ መረብ ግላዊነት ሕጎችን ያካትታሉ።

ii. **<u>የበለጠ ጠንካራ የሆኑ የግዛት ሕጎች፦</u>** ግለሰቡ በ HIPAA ስር ከሚያገኙት የላቀ ሪከርዶች ጋር የመድረስ መብት ሲሰጣቸው ነው የግዛት ሕግ የበለጠ ጠንካራ ነው የሚባለው። እንዲሁም ሪከርዶቹ ከ HIPAA ይልቅ በግዛት ሕግ የበለጠ ጥበቃ በሚያገኙበት ጊዜ የግዛት ሕግ የበለጠ ክልከላ ይኖረዋል። የእኛ የጤና ሚኒስትሪ በጎረቤት ግዛት ለሚኖር ታካሚ የሕክምና እንክብካቤ በሚሰጥበት ጊዜ፣ የበለጠ ጠንካራ ለሆነው ተፈጻሚ የግዛት ሕግ ተገዢ እንሆናለን።

F. **<u>የጤና መረጃ ልውውጥ፦</u>** የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን የጤና ሪከርዶች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ያጋራል ወይም የጤና ሪከርዶችን ከሌሎች HIE ዎች ጋር ከሚለዋወጠው የጤና መረጃ ልውውጦች (Health Information Exchanges, "HIE") ጋር ይለዋወጣል። የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን የጤና መዛግብት ሕክምና እና እንክብካቤ ማስቀጠልን ጨምሮ ለተፈቀዱ አላማዎች ለማጋራት የውሂብ ልውውጥ ቴክኖሎጂ (እንደ የቀጥታ መልዕክት መላላኪያ አገልግሎቶች፣ የጤና መረጃ አገልግሎቶች አቅራቢ (health information services provider, "HISP")፣ እና የአቅራቢ ፖርታሎችን) በኤሌክትሮኒካዊ የጤና ሪከርዱ (Electronic Health Record, "EHR") ጭምር ይጠቀማል። HIE ዎች እና የውሂብ መለዋወጫ ቴክኖሎጂ ለእርስዎ የሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ጥራትን (ለምሳሌ፣ አላስፈላጊ ድርብ ምርመራን ማስወገድ) ለማሻሻል የጤና ሪከርዶችዎን ማጋራትን ያስችላሉ። የሚጋሩ የጤና ሪከርዶች እንደተፈጻሚነቱ፣ እንደ ኤችአይቪ/ኤድስ፣ በግብረስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች፣ የዘረመል መረጃ፣ የአእምሮ ጤና፣ እና የአልኮል/አደንዛዥ ዕጽ አላግባብ ተጠቃሚነት፣ ወዘተ የመሳሰሉ ሚስጢራዊ የዳያግኖሲስ ውጤቶችን ጭምር ያካትታሉ። HIE ዎች እና የውሂብ መለዋወጫ ቴክኖሎጂ አቅራቢዎች እንደ የቢዝነስ አጋሮቻችን ሆነው ይሰራሉ እንዲሁም፣ እኛን በመወከል የእርስዎን PHI ለህክምና፣ ለክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች እና ለተፈቀዱ ሌሎች አላማዎች ያስተላልፋሉ፣ ይዘው ያቆያሉ እና ያስቀምጣሉ። HIE ዎች እና የውሂብ መለዋወጫ ተክኖሎጂዎች የሕክምና መረጃዎትን ሚስጢር እና ምልአት በምክንያታዊ እና ተገቢ መንገድ መጠበቅ የሚያስችሉ አስተዳደራዊ፣ አካላዊ እና ቴክኒካዊ የአደጋ መከላከያዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተፈጻሚነት ያለው ሕግ HIE (ዎች) ላይ ክልከላ የመጣል፣ ፈልጎ የመግባት ወይም ፈልጎ የመውጣት መብቶች ሊሰጥ ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ የጤና ሚኒስትሪ ግላዊነት መኮንናችንን በ 833-718-1043 ያናግሩ ወይም በ privacyofficer@trinity-health.org ኢሜይል ሊልኩልን ይችላሉ።

## II. የተፈቀደ መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ የመስማማት ወይም የመቃወም ዕድል ለዕርስዎ ከመስጠት ጋር

A. **<u>ቤተሰብ/ጓደኞች፦</u>** የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን PHI የሕክምና እንክብካቤዎ ላይ የተሳተፈ ወይም ለዚሁ አላማ ክፍያ አየፈጸመ ለሚገኝ ጓደኛዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል አሳልፎ ይሰጣል። የእርስዎ PHI ለተወሰኑ ወይም ለሁሉም ቤተሰቦችዎ ወይም ጓደኞችዎ እንዳይጋራ የመጠየቅ መብት አሎት። በተጨማሪ፣ የእኛ የጤና ሚኒስትሪ የእርስዎን PHI በአደጋ እርዳታ ጥረቶች ላይ እገዛ በማድረግ ለሚገኝ

ኤጀንሲ ይፋ ያደርጋል፣ ይህንም የሚያደርገው ቤተሰቦችዎ የእርስዎን ሁኔታ፣ ደረጃ፣ እና መገኛ ቦታ በተመለከተ መረጃ እንዲደርሳቸው ነው።

B. **<u>የጤና ሚኒስትሪ –ማውጫ፦</u>** የእኛ ሚኒስትሪ እርስዎ የሆስፒታል ታካሚ በሆኑበት ሁኔታ የተወሰነ እርስዎን የሚመለከት መረጃ ማውጫ ላይ ሊያካትት ይችላል። ይህ መረጃ የእኛ ሚኒስትሪ ላይ የሚገኝ የእርስዎ ስም፣ መገኛ ቦታ፣ የእርስዎ አጠቃላይ ሁኔታ (ለምሳሌ፣ ደህና፣ የተረጋጋ፣ አደገኛ፣ ወዘተ) እና ሃይማኖታዊ ውግንናዎን ያካትታል። ከሃይማኖታዊ ውግንናዎ በስተቀር፣ የማውጫ መረጃው የእርስዎን ስም ጠቅሰው እርስዎን ለማየት ለሚጠይቁ ሰዎች ይፋ ይደረጋል። ስምዎ የእኛ የጤና ሚኒስትሪ ማውጫ ላይ እንዳይካተት የመጠየቅ መብት አሎት። ማውጫው ላይ ላለመካተት ከጠየቁ፣ ለጎብኚዎች የእርስዎን በቦታው መኖር፣ መገኛ ቦታ፣ ወይም አጠቃላይ ሁኔታ ማሳወቅ አንችልም።

C. **<u>መንፈሳዊ እንክብካቤ፦</u>** ሃይማኖታዊ ውግንናዎን ጨምሮ የማውጫ መረጃዎት ስምዎን ባልጠየቁበት ሁኔታ ጭምር ለቤተ-ክህነት አባል ይሰጣል። የመንፈሳዊ እንክብካቤ አቅራቢዎች የጤና እንክብካቤ ቡድን አባላት ናቸው፣ ስለሆነም የእርስዎን እንክብካቤ በተመለከተ ምክር ሊጠየቁ ይችላሉ። ስምዎ ለየትኛውም የቤተ-ክህነት አባል እንዳይሰጥ የመጠየቅ መብት አሎት።

D. **<u>የሚድያ ሪፖርቶች፦</u>** የእርስዎን ስም በመጥቀስ እርስዎን የተመለከተ መረጃ የጠየቀ ሚድያ በሚኖርበት ጊዜ የእኛ ሚኒስትሪ የተቋሙን ማውጫ መረጃ ለሚድያው (ሃይማኖታዊ ውግንናዎትን አስቀርቶ) ይሰጣል። ማውጫው ላይ መካተትን አለመቀበል እንደሚችሉ ልብ ይበሉ።

## III. የእርስዎን ፈቃድ የሚጠይቅ መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ

A. **<u>ማርኬቲንግ፦</u>** የተወሰኑ በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው፣ የእኛ ሚኒስትሪ የሆነ እርስዎ ምርት ወይም አገልግሎት እንዲሸምቱ የሚያበረታቱ ተግባቦቶችን ከእርስዎ ጋር ለማድረግ ወይም የእርስዎን መረጃ ምርቶቻቸውን ወይም አገልግሎቶቻቸውን ለእርስዎ ማቅረብ ለሚፈልጉ ሶስተኛ አካላት አሳልፎ ለመስጠት እንዲፈቀድላቸው እና ለእርስዎ ጉርሻ እንዲከፍሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚጠይቁ አካላት በሚያጋጥሙት ጊዜ እስቀድሞ ከእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

B. **<u>ምርምር፦</u>** የእኛ ሚኒስትሪ ከ HIPAA ወይም ከክሊኒካዊ ምርምር ሕጎች እና ደንቦች ጥያቄ በሚቀርብለት ጊዜ የእርስዎን PHI ለምርምር አላማዎች ይፋ ለማድረግ ከእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ይጠይቃል።

C. **<u>የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎች፦</u>** አብዛኛው ጊዜ የእርስዎን የሳይኮቴራፒ መረጃዎች መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ የእርስዎን የጽሑፍ ፈቃድ ይጠይቃል።

D. **<u>የ PHI ሽያጭ፦</u>** የተወሰኑ በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው፣ PHI መሸጥን የሚጠይቅ ይፋ የማድረግ እርምጃ የእርስዎን የጽሑፍ ፈቃድ ይፈልጋል።

E. **<u>ሌሎች መጠቀሞች ወይም ይፋ ማድረጎች፦</u>** PHI ን በዚህ የግላዊነት አሰራሮች ማሳወቂያ ላልተገለጹ አላማዎች መጠቀሞች ወይም ይፋ ማድረጎች የእርስዎን የጽሑፍ ፈቃድ ይጠይቃሉ (በ HIPAA ካልተፈቀዱ በስተቀር)። የጽሑፍ ፈቃድ የእርስዎን PHI ለምን እየተጠቀምንበት እንደሆነ እንዲያውቁ ይረዳዎታል። የሰጡትን ፈቃድ በየትኛውም ጊዜ የመሰረዝ መብት አሎት።

## IV. በሕበረተሰብ ፖሊሲ ወይም ሕግ የተፈቀዱ ወይም የሚያስገድዱ ያለእርስዎ ፈቃድ መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ

A. **<u>ለሕግ ማስከበር አላማዎች፡-</u>** የኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን PHI በሕግ በተፈቀደው መሰረት ለሕግ አስከባሪ አካላት አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል፣ ለምሳሌ ተጠርጣሪ ወንጀለኛ ለመለየት ወይም ስለ የወንጀል ሰለባ ወይም እርስዎን ስለ ሚጎዳ የወንጀል ተግባር መረጃ ለመስጠት።

B. **<u>በሕግ አስገዳጅነት፡-</u>** የእኛ የጤና ሚኒስትሪ በፌደራል፣ ግዛት፣ ወይም አካባቢ ሕግ ሲጠየቅ የእርስዎን PHI ይፋ ያደርጋል። ምሳሌዎቹ ለፍርድ-ቤት ትእዛዝ/ መጥሪያ ምላሽ መስጠት፣ አስገዳጅ ሪፖርት ለግዛት ማቅረብ (ለምሳሌ፣ በጥይት ተኩስ መቁሰል፣ የህጻናት ብዝበዛ ወይም ቸልተኝነት ሰለባዎች)፣ መንግስታዊ ማጣራቶች፣ ወይም እንደ የሰራተኞች ካሳ ሕጎች ወይም ከተመሳሳይ ሕጎች ጋር ለመስማማት ይፋ ማድረግን ያጠቃልላሉ። የእኛ ሚኒስትሪ የመድሀኒት ቅየራ እና የተጭበረበረ የመድሃኒት ትእዛዝ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለሕግ አስከባሪ እና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች ሪፖርት ያደርጋል።

C. **<u>የሕበረተሰብ ጤና ቁጥጥር ወይም ደህንነት፡-</u>** የእኛ ምኒስትሪ የግለ-ሰብ ወይ የሕብረተሰብ ጤና እና ደህንነት ላይ ያንዣበበ ከባድ ስጋት-አደጋን ለመቀልበስ የእርስዎን PHI ይጠቀማል እንዲሁም ይፋ ያደርጋል። ምሳሌዎች PHI ን የእንክብካቤ ጥራትን በተመለከተ ለግዛት መርማሪዎች ወይም ክትባቶችን፣ ተላላፊ በሽታዎችን በተመለከተ ለሕብረተሰብ ጤና ኤጀንሲዎች ይፋ ማድረግን ወዘተ ያጠቃልላሉ። የእኛ ሚኒስትሪ አሉታዊ ፍጻሜዎችን መሰብሰብ እና ሪፖርት ማድረግ፣ መከታተል፣ የምርቶች መመለስን ማመቻቸት፣ ወዘተ ጨምሮ በ FDA ቁጥጥር ከሚደረግባቸው ምርቶች ወይም እንቅስቃሴዎች ጥራት፣ ደህንነት ወይም ውጤታማነት ጋር በተያያዘ PHI ን ይጠቀማል ወይም ይፋ ያደርጋል።

D. **<u>ሞት አጥኚዎች፣ ሜዲካል መርማሪዎች፣ የቀብር ድሬክተሮች፡-</u>** የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን PHI ለሞት አጥኚ ወይም ለሜዲካል መርማሪ ይፋ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ ይህ የሞተውን ሰው ለይቶ ለማወቅ ወይም የሞት መንስኤ ለማወቅ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን የሕክምና መረጃ ለቀብር ድሬክተሮች ስራዎቻቸውን ይሰሩ ዘንድ ጠቃሚ ስለሚሆን ይፋ ያደርጋል።

E. **<u>የሰውነት አካላት ማቅረብ፡-</u>** የእኛ ሚኒስትሪ PHI ን ለአካል፣ አይን፣ ወይም ቲሹ ልገሳ አላማዎች ሲባል ለሰውነት አካል አቅራቢ ተቋም ይፋ ያደርጋል።

F. **<u>ልዩ የመንግስት ተግባራት፡-</u>** የእኛ ሚኒስትሪ እንደ ወታደራዊ፣ ብሄራዊ ደህንነት እና ስለላ እንቅስቃሴዎች ለመሳሰሉ የመንግስት ተግባራት የእርስዎን PHI ይፋ ያደርጋል። የእኛ ሚኒስትሪ እርስዎ ለአንዳንድ ጥቅማጥቅሞች ብቁ መሆንዎን እና አለመሆንዎን ለመለየት የእርስዎን PHI ለጡር ተመላሽ ጉዳዮች መምሪያ ይጠቀማል ወይም ይፋ ያደርጋል።

G. **<u>ክትባቶች፡-</u>** የእኛ ሚኒስትሪ የክትባት ማረጋገጫ መረጃን አስቀድመው የሚጠይቁ ግዛቶች ወይም ተመሳሳይ ሕግ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ትምህርት-ቤቶች ይፋ ያደርጋል።

## V. የጤና መረጃ መብቶችዎ

የራስዎን PHI በተመለከተ የሚከተሉት የግለሰብ መብቶች አሉዎት፡-

A. **<u>የመፈተሽ እና የመቅዳት መብት፡-</u>** የተወሰኑ በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው፣ እርስዎ የራስዎን PHI የማግኘት እንዲሁም የራስዎን PHI ውሂቡ ከእኛ ጋር እስካለ ድረስ የመፈተሽ እና የመቅዳት መብት አሎት።

የእኛ ሚኒስትሪ እርስዎ የራስዎን PHI ለማግኘት ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ ካደረገ፣ የክልከላውን ምክንያት በጽሑፍ እናሳውቆታለን። ለምሳሌ፣ የሳይኮትየራፒ ማስታወሻዎችን የማግኘት ወይም በሕግ የተከለከለ መረጃ የመፈተሽ መብት የሎትም። ይህ ውሳኔ እንደገና እንዲታይልዎ የመጠየቅ መብት ሊኖሮት ይችላል።

በተጨማሪም የራስዎን PHI በኤሌክትሮኒክ ይዘት እንዲሰጦት የመጠየቅ መብት አሎት፣ ሆኖም ይህ የሚሰራው የእኛ ሚኒስትሪ ኤሌክትሮኒካዊ የጤና ሪከርዶችን የሚጠቀም ከሆነ ነው። በተጨማሪም የእኛ ሚኒስትሪ የታካሚ ፖርታል ካዘጋጀ እርስዎ መረጃውን በዚሁ መንገድ ማግኘት ይችላሉ።

ተፈጻሚ በሆነ የፌደራል ወይም የግዛት ሕግ መሰረት ምክንያታዊ የሆነ የቅጂ ክፍያ ሊጠየቁ ይችላሉ።

ለእርስዎ በሚመች መልኩ፣ የተወሰነ የእርስዎ PHI በታካሚ ፖርታል አማካኝነት እንዲያገኙት ይደረጋል። ተጨማሪ PHI ማግኘት የሚቻለው ጥያቄ በማቅረብ ነው።

**B.** **<u>የማሻሻል መብት፡-</u>** መረጃዎ በእኛ የጤና ሚኒስትሪ እጅ እስካለ ድረስ የራስዎን PHI የማሻሻል መብት አሎት። የራስዎን PHI ላማሻሻል ሲጠይቁ ጥያቄዎትን የጠየቁትን ማሻሻያ ለመደገፍ ምክንያትዎን በማካተት በጽሑፍ ለ privacyofficer@trinity-health.org ወይም፣ ለስርአት ግላዊነት መኮንናችን በ 20555 Victor Parkway Livonia MI 48152 ማቅረብ አለብዎት።

ይሁን እንጂ፣ የእኛ ሚኒስትሪ በሚከተሉት ምክንያቶች የማሻሻያ ጥያቄዎትን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡-

i. የእኛ ሚኒስትሪ የመረጃው ፈጣሪ ካልሆነ፤
ii. መረጃው የተባለው ሪከርድ አካል ካልሆነ፤
iii. መረጃው (በሁኔታው ወይም በባህሪው ምክንያት) ለእርስዎ ፍተሻ ክፍት ካልሆነ፤ ወይም
iv. መረጃው እውነተኛ እና የተሟላ ከሆነ።

የራስዎ PHI ላይ ለውጦች ለማድረግ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ከሆነብዎ፣ የግላዊነት መኮንኑ ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት በጽሑፍ ያሳውቆታል። ውድቀ መደረጉን በመቃወም የጽሑፍ መግለጫ የማቅረብ መብት እንዳሎት ጭምር የግላዊነት መኮንኑ ያሳውቆታል። የእኛ የጤና ሚኒስትሪ እርስዎ ካቀረቡት የለውጥ ማድረግ ጥያቄ በኋላ እርስዎ ለውጥ ሊደረግበት የፈለጉትን መረጃ ይፋ በሚያደርግበት ጊዜ የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን የማሻሻያ ጥያቄ ውድቅ ከተደረገበት ምክንያት ጋር እንዲያካትት መጠየቅ ይችላሉ። የእኛ ሚኒስትሪ የተቃውሞ መግለጫዎትን ውድቅ በማድረግ ውድቅ ያደረገበትን ውሳኔ ቅጂ ሊያቀርብልዎ ይችላል።

**C.** **<u>የአካውንቲንግ መብት፡-</u>** ለሚከተሉት ይፋ ካደረጋቸው ውጪ፣ የእኛ ሚኒስትሪ ይፋ ያደረጋቸውን የእርስዎ PHI የሚመለከት አካውንቲንግ የማግኘት መብት አሎት፡-

i. ሕክምና፣ ክፍያ፣ ወይም የጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች ለማከናወን፤
1. ለእርስዎ፤
2. በእርስዎ ሕክምና ለተሳተፉ ሰዎች፤
3. ለብሄራዊ ደህንነት ወይም ስለላ አላማዎች፤ ወይም
4. ለማረምያ ተቋማት ወይም ለሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት።

ይፋ የተደረጉ የእርስዎን PHI የተመለከተ የአካውንቲንግ ጥያቄዎን በጽሑፍ ለእኛ ሚኒስትሪ በ privacyofficer@trinity-health.org ወይም፣ ለስርአት ግላዊነት መኮንናችን በ 20555 Victor Parkway Livonia MI 48152 ማቅረብ አለብዎ።

የአካውንቲንጉን የጊዜ ክልልም ማካተት አልብዎ፣ ይህም ከ 6 አመት በላይ ሊሆን አይችልም። በየትኛውም የ12-ወር ጊዜ ውስጥ አንድ ጊዜ፣ የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎ PHI ይፋ የተደረገባቸውን ጊዜያት የሚያሳይ አካውንቲንግ በነጻ ይሰጦታል። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተጨማሪ የአካውንቲንግ ጥያቄዎች ከቀረቡ አካውንቲንጉን ለማዘጋጀት ምክንያታዊ ክፍያ የሚከፈልበት ይሆናል።

D. **<u>ክልከላዎችን የመጠየቅ መብት፡-</u>** በአንዳንድ የእርስዎ PHI ለሕክምና፣ ክፍያ ወይም የጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች የመጠቀም ወይም የማጋራት ሁኔታዎች ላይ የተወሰኑ ወይም ሙሉ ክልከላዎች እንዲደረጉ የመጠየቅ መብት አሎት። ይሁን እንጂ፣ የእኛ ሚኒስትሪ ጥያቄዎትን ያየዋል ነገርግን የተጠየቁትን ክልከላዎች ተግባራዊ ለማድረግ የመስማማት ግዴታ የለበትም።

E. **<u>የጤና እቅድ ላይ ክልከላዎች እንዲደረጉ የመጠየቅ መብት፡-</u>** ላገኙዋቸው ነገሮች ወይም አገልግሎቶች ሙሉበሙሉ ከኪስዎ ከሆነ የከፈሉት፣ የእርስዎ PHI ለጤና እቅድ ተላልፎ መሰጠት ላይ (ለክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች) ክልከላ እንዲጣልልዎ የመጠየቅ መብት አሎት። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

F. **<u>የሚስጢራዊ ተግባቦት መብት፡-</u>** የእርስዎን PHI የተመለከቱ ሚስጢራዊ ተግባቦቶችን በአማራጭ መንገዶች ወይም አማራጭ መገኛ ቦታዎች ላይ የመቀበል መብት አሎት። ለምሳሌ፣ የእኛ ሚኒስትሪ እርስዎን ስራ ቦታ ላይ ብቻ ወይም በፖስታ ብቻ እንዲያገኞት መጠየቅ ይችላሉ። ኢሜይልዎን ከሰጡ፣ በሌላ መንገድ እንድናገኞት ጥያቄ ካላቀረቡ በስተቀር የእኛ ሚኒስትሪ በዚሁ ኢሜይል ሊያገኞት ይችላል።

G. **<u>የዚህን ማሳወቂያ ቅጂ የማግኘት መብት፡-</u>** የዚሁ የግላዊነት አሰራሮች ማሳወቂያን የወረቀት ቅጂ በጥያቄዎ መሰረት የማግኘት መብት አሎት።

## VI. አስተማማኝ ደህንነት የሌለው PHI ጥሰት አደጋ

እርስዎን የሚጎዳ የጥሰት አደጋ አስተማማኝ ደህንነት በሌለው PHI ላይ ከተፈጸመ፣ የእኛ ሚኒስትሪ ስለ ጥሰቱ ለእርስዎ የማሳወቅ ግዴታ አለበት። እንደዚህ አይነት ማሳወቂያ እኛን በሚወክሉ የቢዝነስ አጋሮቻችን ሊሰጥ ይችላል።

## VII. የእርስዎን የጤና መረጃ ማጋራት እና በጋራ መጠቀም

የ Trinity Health አባላት፣ የእኛ ሚኒስትሪ እና ሜዲካል ሰራተኞች የጋራ ታካሚዎቻችን በተመለከተ በ HIPAA በተፈቀደው መሰረት የእርስዎን PHI ለሕክምና፣ ለክፍያ እና/ወይም ለጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች ይጠቀሙበታል። ለእርስዎ ሕክምና በምንሰጥበት ሂደት እና የእኛ ሚኒስትሪ የማህበረሰብ ጤና የማሻሻል ተልዕኮ ለማሳካት በምናደርገው ጥረት፣ የእርስዎን PHI ከታች ባሉት ደንቦች ተገዢ ለመሆን ለተስማሙ ሌሎች ድርጅቶች እና አቅራቢዎች እናጋራዋለን፡-

A. **<u>ሜዲካል ሰራተኞች።</u>** ሜዲካል ሰራተኞቹ እና የእኛ ሚኒስትሪ የጤና እንክብካቤ አገልግሎትን በእኛ ሚኒስትሪ ላይ ለእርስዎ ለማቅረብ በተደራጀ የሕክምና ዝግጅት በጋራ ይሳተፋሉ። የእኛ ሚኒስትሪ እና ሜዲካል ሰራተኞቹ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ለእርስዎ በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚፈጠር ወይም የሚቀበሉትን PHI በተመለከተ ለዚህ ማሳወቂያ ደንቦች ተገዢ እንደሚሆኑ ተስማምተዋል። የእኛ ሚኒስትሪ እና የእኛ ሜዲካል ሰራተኞች የእንክብካቤ ጥራትን መገምገም እና ማሻሻልን ጨምሮ የግብረ-ሰናይ ተልዕኮአችንን ለመወጣት የእርስዎን PHI ያገኛሉ እንዲሁም ይጠቀማሉ።

B. **<u>የ Trinity Health አባልነት።</u>** የእኛ ሚኒስትሪ እና ሌሎች የ Trinity Health አባላት ለፍጆታ ግምገማ፣ ለጥራት ግምገማ፣ እና ለተዛማጅ እንቅስቃሴዎች በሚደረግ የተደራጀ የጤና እንክብካቤ ዝግጅት ላይ በጋራ ይሳተፋሉ። እንደ የ Trinity Health አካላት፣ ብሄራዊ የካቶሊክ ጤና እንክብካቤ ስርአት፣ የእኛ የጤና ሚኒስትሪ እና ሌሎች ሆስፒታሎች፣ ነርሲንግ ሆምስ፣ እና የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ላይ የእርስዎን PHI ለፍጆታ ግምገማ፣ ለጥራት ግምገማ፣ እና እናት ኩባንያ ለሆነው Trinity Health እና አባላቶቹ ለተዛማጅ እንቅስቃሴዎች ያጋሩታል። ሁሉም የ Trinity Health አባላት ከፍጆታ ግምገማ እና ከጥራት ግምገማ እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ ከሚፈጠረው ወይም ከሚቀበሉት PHI ጋር በተያያዘ በዚህ ማሳወቂያ ደንቦች ለመገዛት ተስማምተዋል።

እባክዎ የአባል ድርጅቶችን ዝርዝር ለማየት ወደ Trinity Health ድርጣቢያ ይሂዱ http://www.trinity-health.org/። ወይም፣ እንደ አማራጭ፣ ይህን ለመጠየቅ ወደ የግላዊነት መኮንናችን በ 833-718-1043 መደወል፣ ወይም በ privacyofficer@trinity-health.org ኢሜይል ለኛ መላክ ይችላሉ።

C. **<u>የቢዝነስ አጋሮች</u>** የእኛ ሚኒስትሪ የእርስዎን PHI ለእኛ ሚኒስትሪ የተወሰኑ ስራዎችን ለሚሰራልን Trinity Healthን ጨምሮ በእኛ ፋንታ የቢዝነስ ስራዎችን ለመስራት ኮንትራት ለገቡት የቢዝነስ አጋሮች እና ለንኡስ-ኮንትራክተሮቻቸው ያጋራል።

D. **<u>የእርስዎ ጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች እና የእንክብካቤ አስተባባሪዎች</u>** ከእኛ ሚኒስትሪ የሚያገኙት እንክብካቤ በተቀናጀ የእንክብካቤ አውድ ውስጥ ታካሚዎች በተለያዩ አቅራቢዎች በሚታከሙበት እና በብዙ የሕክምና ቦታ ነው፣ ይህ የሕክምና ማስቀጠል እና የተቀናጀ የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ አካል ነው። የእኛ ሚኒስትሪ ሕክምና ለመስጠት፣ ክፍያ ለመቀበል፣ የጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች ለማካሄድ በጋራ ለሚሰሩ ሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች እና የእንክብካቤ አስተባባሪዎች የእርስዎን PHI ያጋራል። የእርስዎ PHI በህክምና መስጠት እና በሕክምና ማስተባበር ለሚሳተፉ አቅራቢዎች በብዙ ኤለክትሮኒካዊ መንገዶች ያጋራል። የእርስዎ PHI ወደ የሌሎች አቅራቢዎች ኤሌክትሮኒካዊ የጤና ሪከርድ ስርአት በቀጥታ ግንኙነት አማካኝነት ሊጋራ ይችላል። የእርስዎ PHI በጤና መረጃ መለዋወጫ ወይም ሌሎች አቅራቢዎች እና የሕክምና አስተባባሪዎች መረጃዎትን እንዲወስዱ በሚያስችል ቴክኖሎጂ አማካኝነት ሊጋራ ይችላል። የእርስዎ PHI ወደ የሌሎች አቅራቢዎች መልዕክት መቀበያ ሳጥኖች በአስተማማኝ መተላለፍያ አማካኝነት ሊጋራ ይችላል።

VIII. **የዚህ ማሳወቂያ ለውጦች።** የእኛ ሚኒስትሪ አሁን ተግባራዊ ለሆነው ማሳወቂያ ደንቦች ተገዢ ይሆናል። የዚህ ማሳወቂያ ደንቦች ላይ ለውጦችን የማድረግ እና አዳዲሶቹ የማሳወቂያው ድንጋጌዎችን በሁሉም በእጃችን የሚገኙ PHI ላይ ተግባራዊ የማድረግ መብት አለን። የእኛ የጤና ሚኒስትሪ ማሳወቂያው ላይ ይየዘት ለውጥ ካደረገ ከማሳወቂያው ማሻሻያ በኋላ እርሰዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጡ የተሻሻለውን ማሳወቂያ ያሰራጫል/ ይሰጦታል። በተጨማሪም የማሳወቂያውን አሁናዊ ቅጂ በየትኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ። አሁናዊ ቅጂዎች የሚኒስትሪው ድረገጽ ላይ ይለጠፋሉ።

ቅሬታዎች። የግላዊነት መብቶችዎ ተጥሰዋል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ወደ የግላዊነት መኮንናችን ወይም ወደ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምርያ ሴክሬታሪ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። ሁሉም ቅሬታዎች በጽሑፍ ቀጥታ ወደ privacyofficer@trinity-health.org ወይም ወደ የስርአት ግላዊነት መኮንናችን በ 20555 Victor Parkway Livonia MI 48152 መቅረብ አለባቸው።

IX. ***ቅሬታ በማቅረብዎ የሚደርስብዎ የበቀል እርምጃ አይኖርም።***

**የግላዊነት መኮንን – ጥያቄዎች / አሳሳቢ ጉዳዮች / ተጨማሪ መረጃ። ጥያቄዎች ካሉት፣ ማንሳት የሚፈልጓቸው ሐሳቦች ካሉት፣ ወይም በግላዊነት አሰራር ማሳወቂያ ላይ ስለተነሱ ጉዳዮች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ወይም ስለ የእኛ የጤና ሚኒስትሪ የግላዊነት ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የግላዊነት መኮንናችንን በ 833-718-1043 ያግኙ፣ ወይም በ privacyofficer@trinity-health.org ኢሜይል ሊልኩልን ይችላሉ።**